**የሰሜን ካሮላይና ግዛት የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ**
**የስደተኞች የጋራ ኃላፊነት ስምምነት**

**እኔ፣ ______________________________፣በ (ኤጀንሲው) የስራ ስምሪት አገልግሎቶች ስር ባሉ በሚከተሉት መስፈርቶች እስማማለሁ:**

- [ ] እኔ የጋራ ኃላፊነት ስምምነት (MRA) እና የድርጊት መርሃ ግብርን ለመከተል ተስማምቻለሁ።
- [ ] እኔ (ከኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ለማግኘት እመዘግባለሁ።
- [ ] እኔ (በኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎቶች በኩል የስራ ቅጥር ተስማሚነት ስልጠና፣ የቋንቋ ስልጠና ወይም ሌላ የስራ ቅጥር ክህሎት በሚሰጥ በማንኛውም የስራ ቅጥር አገልግሎት ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ተስማምቻለሁ።
- [ ] እኔ (በኤጀንሲው) የቅጥር አገልግሎት ሰራተኞች የተያዙ ሁሉንም ቀጠሮዎች አከብራለሁ። በቀጠሮው ሰዓት መገኘት ካልቻልኩ፣ ከተያዘው ቀጠሮ ቢያንስ ሁለት ሰዓት ቀደም ብዬ (ለኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰራተኞች አሳውቃለሁ።
- [ ] እኔ (በኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰራተኞች በተዘጋጁ ማናቸውም የስራ ቃለ መጠይቆች ላይ ለመሳተፍ ተስማምቻለሁ።
- [ ] እኔ (በኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰራተኞች ተገቢ ነው ተብሎ የተወሰነውን ማንኛውንም የስራ ቅጥር ዕድል እቀበላለሁ።
- [ ] እኔ (ከኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ውጭ ሥራ ካገኘሁ ወዲያውኑ (ለኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ሠራተኞችን አሳውቃለሁ።
- [ ] እኔ የስራ ዕድሉን ከተቀበልኩ በኋላ፣ በቅጥር ሂደቱ ወቅት በተስማማሁት መሰረት በስራ መጀመሪያ ቀን በሥራው ላይ እገኛለሁ።
- [ ] ስራ ከመልቀቁ በፊት፣ ከኤጀንሲው የሥራ ስምሪት አገልግሎት ሠራተኞች ጋር እናገራለሁ።
- [ ] ችግር ከተፈጠረ፣ ወይም በዚህ MRA ውስጥ የተዘረዘሩት ተግባራት እንዳላከናውን የሚከለክሉኝ ለውጦች ከተፈጠሩ ለ (ኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ቢሮ ወዲያውኑ አሳውቃለሁ። MRA ውን አለማክበር የ (ኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት መጠን እንዲቀንስ ወይም እንዲቋረጥ ሊያደርግ ይችላል።
- [ ] ያለ በቂ ምክንያት፣ በፍቃዴ ስራዬን አላቋርጥም/አላቆምም።
- [ ] በፈቃዴ ሥራዬን ካቆምኩ ወይም የጋራ ኃላፊነት ስምምነቱን ካጣስኩ ከ (ኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት እንደምታገድ ተረድቻለሁ።
- [ ] በፈቃዴ ስራዬን ካቆምኩ ወይም የጋራ ኃላፊነት ስምምነቱን ከጣስኩ፣ የስራ ቅጥር አገልግሎቶቹ ወደ ነበሩበት ከመመለሳቸው በፊት የድርጊት መርሃ ግብር ተግበራዊ መሆን እንዳለበት ተረድቻለሁ።
- [ ] በፈቃዴ ስራዬን ካቆምኩ ወይም የጋራ ኃላፊነት ስምምነቱን ከጣስኩ፣ በኤጀንሲው የስራ ስምሪት አገልግሎት ባለሙያ በተገለፀልኝ መሰረት የድርጊት መርሃ ግብር እስካልተገበርኩ ድረስ ስሜ በ (ኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ዝርዝር ግርጌ ላይ እንደሚቀመጥ ተረድቻለሁ።
- [ ] በፈቃዴ ስራ ካቆምኩ፣ ያለማስጠንቀቂያ ስራ ከለቀቅኩ፣ ወይም (ኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ሠራተኛ የሚሰጠኝ የስራ ዕድልን ውድቅ ካደረኩ፣ የማኅበራዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት ይህን እንዲያውቅ እንደሚደረግ፣ የማገኘውም ጥቅማጥቅሞች ሊቀንሱ ወይም ሊቋረጡ እንደሚችሉ ተረድቻለሁ።

**የ (ኤጀንሲው) የስራ ቅጥር አገልግሎት ሰራተኞች እርስዎ ስራ እንዲያገኙ እና ስራዎን ይዘው እንዲቆዩ በሚከተሉት መንገዶች ለመርዳት ተስማምተዋል:**

- የፌዴራል ወይም የስቴት ዝቅተኛው የደመወዝ መጠንን የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደሞዞች ወደሚከፍሉ ተገቢ የስራ ቅጥር እድሎች እርስዎን በመምራት/ሪፈር በማድረግ።
- መደበኛ/የተለመደ ዕለታዊ እና ሳምንታዊ የስራ ሰዓቶች ወደአላቸው የሥራ ዕድሎች እርስዎን በመምራት/ሪፈር በማድረግ።
- ችሎታዎን መሰረት ያደረጉ በመደበኛነት ማከናወን ወደሚችሏቸው የስራ እድሎች ብቻ እርስዎን በመምራት/ሪፈር በማድረግ።
- ተስማሚ የእለት ተእለት የመጓጓዣ ጊዜ ወዳላቸው እና ካልዎት ማንኛውም አስፈላጊ የልጅ እንክብካቤ ፍላጎት ጋር ወደ የሚጣጣሙ የስራ ዕድሎች እርስዎን በመምራት/ሪፈር በማድረግ።
- ሁሉንም ተገቢ የጤና እና የደህንነት መመዘኛዎችን ወደሚያሟሉ የስራ ዕድሎች እርስዎን በመምራት/ሪፈር በማድረግ።
- በስራ ቦታዎቻቸው ላይ በእድሜ፣ በፆታ፣ በዘር፣ በሀይማኖት፣ በቀለም ወይም በትውልድ ሀገር ሊደርስ የሚችል መድልዎን በፖሊሲዎቻቸው ወደማይፈቅዱ የስራ እድሎች እርስዎን በመምራት/ሪፈር በማድረግ።
- በ MRA እና/ወይም በድርጊት መርሃ ግብሩ ላይ በተገለፀው መሰረት እንደ የህፃናት እንክብካቤ፣ የመጓጓዣ እና ወዘተ ያሉ አገልግሎቶችን በማቀናጀት እገዛ በማድረግ።
- በኢኮኖሚ እራስዎን እንዲችሉ ለመርዳት ወደ ሌሎች የማህበረሰብ አገልግሎቶች እና ግብዓቶች በመላክ/ሪፈር ማድረግ።
- በ (ኤጀንሲው) የስራ ስምሪት አገልግሎት ሰራተኞች በተለየው መሰረት በስራ ቅጥር ስልጠና፣ በቋንቋ ስልጠና ወይም በሌላ የቅጥር ክህሎቶች ላይ በማገዝ/በመርዳት።
- የድርጊት መርሃ ግብሩ መዘመን ወይም መለወጥ ሲያስፈልግ ከእርስዎ ጋር በመደራደር።
- እነዚህን ፖሊሲዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ በቃል አስተርጓሚ ወይም በፅሑፍ ትርጉም በማቅረብ።
- የስቴቱን/የግዛቱን የስደተኞች ፕሮግራም የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ፖሊሲን ቅጂ ለእርስዎ በመስጠት።

ከእኔ የሚጠበቀውን ነገር ተረድቻለሁ። በስደተኞች አገልግሎት መርሃ ግብር ፖሊሲ/መመሪያው ላይ እንደተገለጸው በቂ ምክንያት ሳይኖረኝ፣ መመሪያ አለማክበር/መጣስ ከ (ኤጀንሲው) የማገኘው የስራ የቅጥር አገልግሎቶች እንዲቋረጡ ሊያደርግ እንደሚችል ተረድቻለሁ።
እንዲሁም በ ሰ(ኤጀንሲው) ስራ ስምሪት አገልግሎት ባለሙያዎች/ሰራተኞች በሚወሰዱብኝ እርምጃዎች ላይ ይግባኝ የመጠየቅ መብት እንዳለኝ ተረድቻለሁ።

ባለጉዳይ ______________________________ ______________
(ፊርማ) (ቀን)

የስደተና መለያ ቁጥር ______________________________

የ (ኤጀንሲው) የስራ ስምሪት አገልግሎት ሰራተኞች/ባለሙያዎች ______________________________ ______________
(ፊርማ) (ቀን)

ርዕስ ______________________________

የቋንቋ አስርጓሚው ፊርማ ______________________________ ወይም ትርጉም ተያይዟል ☐

***ቅፁን ለመሙላት የሚረዳ መመሪያ***
***የሰሜን ካሮላይና ግዛት የሲደተኞች ጉዳይ ቢሮ***
***የሲደተኞች የጋራ ኃላፊነት ስምምነት***

***ዓላማ:***
የዚህ ቅጽ ዓላማ ደንበኛው ከኤጀንሲው ጋር ወደ ለስራ ቅጥር ተስማሚነት እቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ሲገቡ ከሁለቱንም አካላት ምን እንደሚጠበቅ እና ያለባቸውን ሀላፊነቶች በግልፅ የሚገልጽ መሳሪያ ማቅረብ ነው። ቅጹን መሞላት ያለበት የስራ ቅጥር አገልግሎቶችን የማስተባበር ኃላፊነት ባለበት የስደተኞች ኤጀንሲ የስራ ባልደረባ/ባለሙያ ነው። የጋራ ሃላፊነት ስምምነት ከስራ ቅጥር ተስማሚነት ዕቅድ (DSS-6232) ጋር በባለጉዳዩ ፋይል ውስጥ መካተት አለበት።

***መመሪያዎች:***

- ባለጉዳዮች በገጽ አንድ ላይ የተዘረዘሩትን ኃላፊነቶች መረዳታቸውን ለማመልከት የስማቸውን የመጀመሪያ ፊደላት (በተለይም አጭር ፊርማ) በእያንዳንዱ መስመር አጠገብ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው።
- የኤጀንሲው ሰራተኞች ኤጀንሲው ያለበትን ሃላፊነት ለባለጉዳዩ ማስረዳት ያለባቸው ሲሆን፣ በገጽ ሁለት ላይ ከኤጀንሲው ሰራተኞች ፊርማ እና ቀን አጠገብ ባለጉዳዩም ፊርማ እና ቀን ማስቀመጥ አለበት።
- የጋራ ሃላፊነት ስምምነት ሰነዱ ለባለጉዳዩ ከተብራራ እና ከተረጎመ በኋላ አስተርጓሚው በሰነዱ ላይ መፈረሙን ያረጋግጡ። የትርጉም አገልግሎት አስፈላጊ ካልነበረ፣ እባክዎን N/A ብለው ይፃፉ።

***<u>ማስታወሻ:</u>*** የስደተኞች የጋራ ኃላፊነት ስምምነት ቅፅን ሞልተው የሚያጠናቅቁ የአገልግሎት አቅራቢው ባለሙያዎች/ሰራተኞች ቅፁ ተሞልቶ ሲጠናቀቅ ደንበኛው የቅፁን ቅጂ መቀበሉን ማረጋገጥ አለባቸው።